የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ – ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 4
Addis Ababa 20th October, 2004

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬/፲፱፻፺፯ ዓ·ም·
"የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.. ገጽ ፪ሺ፱፻፲፰

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬/፲፱፻፺፯
## ስለኢሚግሬሽን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩· "የቤተሰብ አባል" ማለት የአንድ ሰው የትዳር ጓደኛ ወይም በሥሩ የሚተዳደር ልጅ ወይም ጥገኛ የሆነ ሌላ ሰው ነው፤

፪· "መደበኛ መኖሪያ ቦታ" ማለት በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፩፻፹፫ የተደነገገውን ትርጓሜ የሚያሟላ የአንድ ሰው መኖሪያ ቦታ ነው፤

፫· "ባለሥልጣን" ማለት የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፤

፬· "ሚኒስቴር" ማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤

፭· "አዋጅ" ማለት የኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፲፱፻፺፮ ነው።

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 114/2004
"Immigration Council of Ministers Regulations Page 2918

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 114/2004*
## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON IMMIGRATION*

This Regulation are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 21 of the Immigration proclamation No. 354/2004

### *PART ONE*
### *GENERAL*

1. *Short title*

This Regulation may be cited as the "Immigration Council of Ministers Regulation No. 114/2004".

2. *Definitions*

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1) "Member of a Family" means the spouse of , or a child or any other person who is dependent on, a person;
2) "Domicile" means the residence of a person as defined under Article 183 of the Civil Code of Ethiopia;
3) "Authority" means the Security, Immigration and Refugee Affairs Authority;
4) "Ministry" means the Ministry of Foreign Affairs;
5) "Proclamation" means the Immigration proclamation No. 354/2003

ያንዱ ዋጋ 4.40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

## ክፍል ሁለት
## ስለጉዞ ሰነዶች አሰጣጥ ሁኔታ

፫· የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት

፩· የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ለሚከተሉት ይሰጣል፤

ሀ) በውጭ አገር በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቋሚ መልዕክተኛ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ለሚመደቡ አምባሳደሮች፣ የዲፕሎማቲክ ወኪሎች፣ አታሼዎች፣ የቆንስላ ወኪሎች እና ለነዚሁ የትዳር ጓዶች፤

ለ) የኢትዮጵያ መንግሥትን በመወከል በጉባዔ ወይም በስብሰባ ለመሳተፍ ወይም ለሌላ የመንግሥት ሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ደረጃቸው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰን መልዕክተኞች፤

ሐ) በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ደረጃቸው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰን የመንግሥት ባለሥልጣኖች፤

መ) በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ለሚሠሩና የዲፕሎማቲክ ደረጃ ላላቸው ኢትዮጵያውያን እና ለነዚሁ የትዳር ጓደኞች፤

ሠ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከፍተኛ ክብር ለሚሰጣቸው ሰዎች።

፪· የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንዲሰጥ ጉዳዩ የሚመለከተው መሥሪያ ቤት ወይም እንደ ሁኔታው አመልካቹ ራሱ ለሚኒስቴሩ በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ለማሰጠት የሚያበቃው ምክንያት በግልጽ መጠቀስ አለበት።

፬· ሰርቪስ ፓስፖርት

፩· ሰርቪስ ፓስፖርት ለሚከተሉት ይሰጣል፤

ሀ) በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቋሚ መልክተኛ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤቶች በሠራተኛነት ለሚመደቡ ኢትዮጵያውያን፤

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ላልተመለከቱና ለመንግሥት ሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን፤

ሐ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ/ መሠረት የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ለተሰጣቸው ሰዎች ቤተሰብ አባላት፤

መ) በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሚሠሩና ኢትዮጵያዊ ለሆኑ ዓለም አቀፍ ሲቪል ሠራተኞች እና ለነዚሁ የትዳር ጓደኞች፤

፪· ሰርቪስ ፓስፖርት እንዲሰጥ ጉዳዩ የሚመለከተው መሥሪያ ቤት ወይም እንደ ሁኔታው አመልካቹ ራሱ ለሚኒስቴሩ በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ ሰርቪስ ፓስፖርት ለማሰጠት የሚያበቃው ምክንያት በግልጽ መጠቀስ አለበት።

፭· መደበኛ ፓስፖርት

መደበኛ ፓስፖርት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሲያመለክት ይሰጣል።

፮· የሐጂና ኡምራ ፓስፖርት

ለሐጂና ኡምራ ፀሎት ተጓዦች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሐጂና ኡምራ ፓስፖርት ሊሰጥ ይችላል።

፯· የውጭ አገር ሰው ፓስፖርት

የውጭ አገር ሰው ፓስፖርት በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነና ከአገሩ መንግሥት የጉዞ ሰነድ ለመቀበል ላልቻለ የውጭ አገር ሰው ወይም ዜግነት ለሌለው ሰው ይሰጣል።

## PART TWO
## Issuance of Travel Documents

3. *Diplomatic Passport*

1) Diplomatic passports shall be issued to:
   (a) ambassadors, diplomatic agents, attaches and consular representatives who are assigned in the Ethiopian Embassies, Permanent Missions and Counsular Posts abroad and to their spouses;
   (b) Ethiopian government envoys holding such ranks as may be specified by directives of the Ministry and who travel abroad to participate in conferences or meetings or for other government business;
   (c) government officials holding such ranks as may be specified by directives of the Ministry and who travel abroad for various purposes;
   (d) Ethiopian employees of international and regional organizations with the rank of diplomatic status and their spouses; and
   (e) distinguished dignitaries specified as such by directives of the Ministry.
2) Any application to be submitted to the Ministry, for the issuance of a diplomatic passport, by the concerned government office or the applicant himself, shall specify the grounds that qualify the applicant for the grant of such passport.

4. *Service Passport*

1) Service passports shall be issued to:
   (a) Ethiopians assigned, as staff members, in Ethiopian Embassies, and Permanent Missions and Consular Posts abroad;
   (b) Ethiopiians, other than those specified under Article 3 of these Regulations, who travel abroad for government business;
   (c) the family members of persons holding diplomatic passports pursuant to sub-article 1 (a) of Article 3 of these Regulations;
   d) Ethiopians who are employees of international or regional organizations with international civil servant's status and their spouses.
2) Any application to be submitted to the Ministry, for the issuance of service passport, by the concerned government office or the applicant himself, shall specify the grounds that qualify the applicant for the grant of such passport.

5. *Ordinary Passport*

Ordinary passport shall be issued to any Ethiopian upon request.

6. *Hajj and Umrah Passport*

Hajj and Umrah passport may, where necessary, be issued to Hajj and Umrah pilgrims.

7. *Alien Passport*

An alien passport shall be issued to a resident foreigner who is unable to obtain his national travel document or who is stateless.

፰· የይለፍ ሰነድ

የይለፍ ሰነድ ፓስፖርት ለሌለውና ከውጭ ወደ አገሩ ለሚመለስ ኢትዮጵያዊ ይሰጣል።

፱· አስቸኳይ የጉዞ ሰነድ

፩· አስቸኳይ የጉዞ ሰነድ ከኢትዮጵያ ለሚወጣና ከአገሩ መንግሥት የጉዞ ሰነድ ለመቀበል ላልቻለ የውጭ አገር ሰው ወይም ዜግነት ለሌለው ሰው ይሰጣል።

፪· የአስቸኳይ የጉዞ ሰነድ የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ መውጫ ብቻ ነው።

፲· የስደተኞች የጉዞ ሰነድ

፩· የስደተኞች የጉዞ ሰነድ ኢትዮጵያ ውስጥ በስደተኛነት ለታወቁ ሰዎች ይሰጣል።

፪· የስደተኞች የጉዞ ሰነድ ለመውጫ ብቻ ወይም ለደርሶ መልስ ሊሰጥ ይችላል።

፲፩· የጉዞ ሰነዶች ፀንተው ስለሚቆዩበት ጊዜ

፩· የጉዞ ሰነዶች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ......... አምስት ዓመት

ለ) ሰርቪስ ፓስፖርት .................. አምስት ዓመት

ሐ) መደበኛ ፓስፖርት ................. አምስት ዓመት

መ) የሐጂና ኡምራ ፓስፖርት .......... አንድ ዓመት

ሠ) የውጭ አገር ሰው ፓስፖርት ....... አንድ ዓመት

ረ) የይለፍ ሰነድ ....................... እስከ ስድስት ወር

ሰ) አስቸኳይ የጉዞ ሰነድ ............. እስከ ሦስት ወር

ሸ) የስደተኞች የጉዞ ሰነድ .............. አንድ ዓመት

፪· የጉዞ ሰነድ ሲጠፋ፣ ሲበላሽ ወይም ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ በአዲስ የጉዞ ሰነድ እንዲተካ መጠየቅ ይቻላል።

፲፪· የጉዞ ሰነዶች ዝግጅት

፩· የሁሉንም ዓይነት የጉዞ ሰነዶች ቅርጽና ይዘት የመወሰንና የማሳተም ኃላፊነት የባለሥልጣኑ ይሆናል። ሆኖም የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶችን በሚመለከት ባለሥልጣኑ በቅድሚያ ከሚኒስቴሩ ጋር መመካከር አለበት።

፪· የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች የሚሰጡት በሚኒስቴሩ ቢሆንም ለእያንዳንዱ አመልካች ለመስጠት የሚዘጋጁት በባለሥልጣኑ ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## ስለቪዛዎች አሰጣጥ ሁኔታ

፲፫· ጠቅላላ

በዚህ ደንብ መሠረት ማንኛውም የመግቢያ ቪዛ ከመሰጠቱ በፊት ጠያቂው በአዋጁ አንቀጽ ፭ መሠረት ቪዛ የሚያስከለክለው ሁኔታ አለመኖሩ መረጋገጥ አለበት።

፲፬· የዲፕሎማቲክ ቪዛ

፩· ዲፕሎማቲክ ቪዛ ለሚከተሉት የውጭ አገር ሰዎች ይሰጣል፤

ሀ) በኢትዮጵያ በሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎችና ቋሚ መልእክተኛ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ለሚመደቡ አምባሳደሮች፣ የዲፕሎማቲክ ወኪሎች፣ አታሼዎች፣ የቆንስላ ወኪሎች እና ለእነዚሁ የትዳር ጓደኞች፣

ለ) የዲፕሎማቲክ ደረጃ ላላቸው ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ የሆኑ የዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ድርጅቶች ኃላፊዎችና ለእነዚሁ የትዳር ጓደኞች፤

ሐ) ለመንግሥት ሥራ ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡ ወይም ኢትዮጵያን አቋርጠው ወደ ሌላ አገር ለሚሄዱ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ለያዙ የውጭ አገር ሰዎች።

8. *Laissez-Passer*

Laissez-passer shall be issued to an Ethiopian who is not holding a passport and is returning from abroad.

9. *Emergency Travel Document*

1) An emergency travel document shall be issued to a foreigner who is unable to obtain his national travel document or who is stateless and is departing from Ethiopia.
2) An emergency travel document shall be issued for exit only.

10. *Refugee Travel Document*

1) Refugee travel documents shall be issued to persons recognized as refugees in Ethiopia.
2) A refugee travel document may be issued either for exit only or for re-entry.

11. *Validity of Travel Documents*

1) The validity of travel documents shall be as follows:
   (a) diplomatic passport............................. 5 years;
   (b) service passport .................................. 5 years
   (c) ordinary passport ................................. 5 years
   (d) Hajj and Umrah passport........................ 1 year
   (e) Alien passport ........................................ 1 year
   (f) laissez-passer .......................... up to 6 months
   (g) emergency travel document ... up to 3 months
   (h) refugee travel document ........................ 1 year
2) A request for the replacement of any travel document may be submitted where the docment is lost or damaged or where its validity period expires.

12. *Preparation of Travel Documents*

1) The Authority shall be responsible for the determination of the form and content of all travel documents and for their production; provided, however, that it shall conduct prior consultation with the Ministry with regard to diplomatic and service passports.
2) Notwithstanding the power of the Ministry to issue diplomatic and service passports, the passport to be issued to each applicant shall be prepared by the Authority.

## *PART THREE*
## *ISSUANCE OF VISAS*

13. *General*

Prior to the issuance of any visa in accordance with this Regulation, the non-existence of conditions warranting refusal thereof as provided for in Article 5 of the proclamation should be ascertained.

14. *Diplomatic Visa*

1. Diplomatic visas shall be issued to the following foreigners:
   (a) ambassadors, diplomatic agents, attaches and consular representatives who are assigned in foreign embassies, permanent missions and consular posts in Ethiopia and to their spouses;
   (b) officials, having diplomatic status, of international and regional organizations having their seats in Ethiopia, and to their spouses,
   (c) foreigners holding diplomatic passports and coming to or transiting through Ethiopia for government business.

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ዲፕሎማቲክ ቪዛ የሚሰጠው ከጠያቂው አገር የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ ኤምባሲ፣ ቋሚ መልዕክተኛ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም ከሚመለከተው ዓለም አቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ድርጅት የዲፕሎማቲክ ኖት ሲቀርብ ነው።

፲፭· ሰርቪስ ቪዛ

፩· ሰርቪስ ቪዛ ለሚከተሉት የውጭ አገር ሰዎች ይሰጣል፤

ሀ) በኢትዮጵያ በሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎችና ቋሚ መልእክተኛና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ በቋሚነት ተመድበው ለሚሰሩና ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ ሠራተኞችና ለቤተሰቦቻቸው አባላት፤

ለ) ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ በሆኑ ዓለም አቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ድርጅቶች ውስጥ ተመድበው ለሚሠሩ የዓለም አቀፍ ሲቪል ሠራተኞች እና ለቤተሰቦቻቸው አባላት፤

ሐ) ለመንግሥት ሥራ ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡ ወይም ኢትዮጵያን አቋርጠው ወደ ሌላ አገር ለሚሄዱ ሰርቪስ ፓስፖርት ለያዙ የውጭ አገር ሰዎች፤

መ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬/፩/ (ሀ) እና (ለ) መሠረት የዲፕሎማቲክ ቪዛ ለሚሰጣቸው ሰዎች ቤተሰብ አባላት።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ሰርቪስ ቪዛ የሚሰጠው ከጠያቂው አገር የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ ኤምባሲ፣ ቋሚ መልዕክተኛ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም ከሚመለከተው ዓለም አቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ድርጅት የዲፕሎማቲክ ኖት ሲቀርብ ነው።

፲፮· የሥራ ቪዛ

፩· የሥራ ቪዛ በሚከተሉት ምክንያቶች ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ የውጭ አገር ሰዎች ይሰጣል፤

ሀ) በኢንቨስትመንት ሥራ ለመሰማራት፤

ለ) የሥራ ፈቃድን በሚመለከት አግባብ ባለው ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማንኛውም የሥራ መስክ ተቀጥረው ለመሥራት፤

ሐ) ከውጭ አገር መንግሥት፣ ከዓለም አቀፍ ወይም አህጉራዊ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት የተለያዩ ሥራዎች ለመሥራት፤

መ) ለበጎ አድራጎት ሥራ ያለደመወዝ ለማገልገል፤

ሠ) ኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ ሲምፖዚየም፣ ኢግዚቢሽን፣ ዓውደ ጥናት ወይም በመሳሰሉት ዝግጅቶች ለመሳተፍ ወይም ሥልጠና ለመስጠት፤

ረ) ለጥናትና ምርምር፤

ሰ) ለመገናኛ ብዙኃን ሥራ።

፪· የሥራ ቪዛ ለአንድ ጊዜ መግቢያ ወይም ለብዙ ጊዜ መመላለሻ እንዲያገለግል ሊሰጥ ይችላል።

፲፯· የመኖሪያ ቪዛ

የመኖሪያ ቪዛ የሚሰጠው ለሚከተሉት ይሆናል፤

፩· በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለሚመጡ በኢትዮጵያዊያን ጉዲፈቻ ለተደረጉ ወይም ከኢትዮጵያ ዜጎች ጋር የፀና ጋብቻ ላላቸው የውጭ አገር ሰዎችና ለቤተሰቦቻቸው አባላት፤

፪· ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖሩ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ለተሰጣቸው የውጭ አገር ሰዎች ቤተሰብ አባላት፤

፫· ጥቅም የሚያገኙበትን ማናቸውንም ሥራ ሳይሠሩና ለአገሪቱ ሸክም ሳይሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለሚመጡ የውጭ አገር ሰዎችና ለቤተሰቦቻቸው አባላት።



2) Diplomatic visa shall be issued pursuant to sub-article (1) of this Article only where a diplomatic note from the department of foreign affairs, embassy or consular posts of the requesting state or from the concerned international or regional organization has been presented.

15. Service Visa

1) Service visas shall be issued to the following foreigners:
   (a) permanent employees of foreign embassies, permanent missions and consular posts in Ethiopia who are holding service passports and to members of their families;
   (b) international civil servants assigned in international or regional organizations having their seats in Ethiopia and to members of their families;
   (c) foreigners holding service passports and coming to or transiting through Ethiopia for government business;
   (d) the family members of persons issued with diplomatic visas pursuant to Article 14 (1) (a) and (b) of these Regulations.
2) Service visa shall be issued in accordance with sub-article (1) of this Article only where a diplomatic note from the department of foreign affairs, embassy or consular post of the requesting state or from the concerned international or regional organization has been presented.

*16. Business visa*

1) Business visa shall be issued to foreigners who are coming to Ethiopia:
   (a) for investment activities;
   (b) without prejudice to the provisions of the relevant law concerning work permits, for employment in any activity;
   (c) for various activities to be carried out in accordance with an agreement entered into with a foreign government, an international or regional organization or non-governmental organization;
   (d) for humanitarian service without remuneration;
   (e) for participation in symposia, exhibitions, workshops and similar activities to be held in Ethiopia or for giving a training;
   (f) for study and research;
   (g) for mass media activities.
2) Business visa may be issued for single or multiple entry.

*17. Immigrant Visa*

Immigrant visas shall be issued to the following:

1) Foreigners who have been adopted by Ethioians or who have valid marriages with Ethiopians and are coming to reside in Ethiopia, and to members of their families;
2) Family members of foreigners holding permanent resident permits in Ethiopia;
3) Foreigners coming to reside in Ethiopia without either being engaged in any gainful activities or becoming public burden, and to members of their families.

፲፰· የቱሪስት ቪዛ

፩· የቱሪስት ቪዛ የሚሰጠው ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ የውጭ አገር ሰዎች ይሆናል።

፪· የቱሪስት ቪዛ ከመሰጠቱ በፊት በአዋጁ አንቀጽ ፫/፪/ የተደነገጉት ሁኔታዎች መሟላታቸው መረጋገጥ አለበት።

፫· የቱሪስት ቪዛ ለአንድ ጊዜ መግቢያ ወይም ለብዙ ጊዜ መመላለሻ እንዲያገለግል ሊሰጥ ይችላል።

፬· በቱሪስት ቪዛ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም ሥራ እንዲሠራ አይፈቀድለትም።

፲፱· የትራንዚት ቪዛ

፩· የትራንዚት ቪዛ የሚሰጠው ኢትዮጵያን አቋርጦ ወደሌላ አገር ለሚሄድ የውጭ አገር ሰው ነው።

፪· የትራንዚት ቪዛ ከመሰጠቱ በፊት በአዋጁ አንቀጽ ፫/፪/ የተደነገጉት ሁኔታዎች መሟላታቸው መረጋገጥ አለበት።

፫· የትራንዚት ቪዛ ለአንድ ጊዜ ወይም ለደርሶ መልስ ትራንዚት እንዲያገለግል ተደርጎ ሊሰጥ ይችላል።

፳· የተማሪ ቪዛ

፩· የተማሪ ቪዛ የሚሰጠው ለትምህርት ወይም ለሥልጠና ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጣ የውጭ አገር ሰው ይሆናል።

፪· የተማሪ ቪዛ ከመሰጠቱ በፊት፣

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርቱን ወይም ሥልጠናውን የሚሰጠው የትምህርት ተቋም የተቀበለው ስለመሆኑ፣ እና

ለ) የትምህርትና የመኖሪያ ወጪው ስለሚሸፈንበት ሁኔታ፣ የሚገልጽ ማረጋገጫ ጠያቂው ማቅረብ አለበት።

፳፩· ቪዛዎች ፀንተው ስለሚቆዩበት ጊዜ

፩· የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ቪዛዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፪· ሌሎች ቪዛዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

## ክፍል አራት

## የጉዞ ሰነዶችንና ቪዛዎችን ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፳፪· የጉዞ ሰነዶችን ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩· የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርት ለማግኘት ማመልከቻ የሚቀርበው ለሚኒስቴሩ ይሆናል። ሚኒስቴሩ ማመልከቻውን መርምሮ ፓስፖርቱ እንዲሰጥ ሲወስን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ለፓስፖርቱ ዝግጅት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ያስተላልፋል።

፪· የይለፍ ሰነድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚቀርበው ለኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ይሆናል።

፫· የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፬ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ሌሎች የጉዞ ሰነዶችን ለማግኘት ማመልከቻ የሚቀርበው ለባለሥልጣኑ ይሆናል።

፬· የጉዞ ሰነዶችን ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶና አግባብ ባለው አካል ከተሰጠ መታወቂያ ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፭· አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ከተመለከቱት በተጨማሪ ፎቶግራፉንና የጣት አሻራውን መስጠት አለበት።

18. *Tourist Visa*

1) Tourist visas shall be issued to foreigners who are coming to visit Ethiopia.
2) Prior to the issuance of a tourist visa, it has to be ascertained that the requirements specified under Article 3(2) of the proclamation have been met.
3) A tourist visa may be issued for single or multiple entry.
4) Any foreigner who has entered Ethiopia by a tourist visa may not be allowed to work in Ethiopia.

19. *Transit Visa*

1) Transit visa shall be issued to a foreigner who is traveling to another country across Ethiopia.
2) Prior to the issuance of a transit visa, it has to be ascertained that the requirements specified under Article 3(2) of the proclamation have been m .
3) A transit visa may be issued for either single or double transit.

20. *student Visa*

1) Student visa shall be issued to a foreigner who is coming to Ethiopia for education or training.
2) Prior to the issuance of a student visa the applicant shall be required to produce evidence showing:
   (a) his admission to an educational or training institution in Ethiopia; and
   (b) the financial means to cover his educational and accommodation expenses.

21. *Validity of Visas*

1) Validity periods of diplomatic and service visas shall be determined in accordance with directives to be issued by the Ministry.
2) Validity periods of other visas shall be determined in accordance with directives to be issued by the Authority.

## PART FOUR

## APPLICATION FOR TRAVEL DOCUMENTS AND VISAS

22. *Application for Travel Documents*

1) Applications for the issuance of diplomatic and service passports shall be submitted to the Ministry. The Ministry shall, upon examining the application and authorizing the issuance of the passport, transmit to the Authority the information required for the preparation of the passport pursuant to Article 12 of this Regulation.
2) Applications for the issuance of laissez-passer shall be submitted to Ethiopian Embassies and Consular Posts abroad.
3) Wothout prejudice to the provisions of Article 24 of this Regulation, applications for the issuance of other travel documents shall be submitted to the Authority.
4) An application for a travel document shall be made by filling in a form issued for such purpose and shall be accompanied with an identity card issued by the appropriate organ.
5) The applicant shall, in addition to those require under Sub-Article (4) of this Article, furnish his photograph and finger print.

፳፫· ቪዛዎችን ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩· የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ቪዛዎች ለማግኘት ማመልከቻዎች የሚቀርቡት ለሚኒስቴሩ ወይም ለኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ይሆናል።

፪· ሌሎች ቪዛዎችን ለማግኘት ማመልከቻዎች የሚቀርቡት ለባለሥልጣኑ ወይም ለኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቆንስላ ጽ/ቤቶች ይሆናል።

፫· ቪዛን ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶና ከጸና የጉዞ ሰነድን እንደአስፈላጊነቱ ከጸና የጤና የምስክር ወረቀት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፳፬· የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች የጉዞ ሰነዶችንና ቪዛዎችን ስለሚሰጡበት ሁኔታ

፩· የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች፣

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ መሠረት የይለፍ ሰነድ ይሰጣሉ፤

ለ) ከይለፍ ሰነድ እና ከዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች በስተቀር ሌሎች የጉዞ ሰነዶችን በሚመለከት የሚቀርቡላቸውን ማመልከቻዎች ተቀብለው መሟላታቸውን ሲያረጋግጡ ለባለሥልጣኑ ያስተላልፋሉ፤ የጉዞ ሰነዶቹ በባለሥልጣኑ ተዘጋጅተው ሲላኩላቸውም ለአመልካቾቹ ይሰጣሉ።

፪· የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፰ መሠረት በሚኒስቴሩና በባለሥልጣኑ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል ቪዛዎችን ይሰጣሉ።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌ ቢኖርም የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች የመኖሪያ ቪዛ ወይም የተማሪ ቪዛ ከመስጠታቸው በፊት የባለሥልጣኑን ስምምነት ማግኘት አለባቸው።

፳፭· በመግቢያ በሮች ላይ ቪዛ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

በመግቢያ በሮች ላይ ቪዛ ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፰ መሠረት ሚኒስቴሩና ባለሥልጣኑ በሚያወጧቸው መመሪያዎች ይወሰናሉ።

## ክፍል አምስት
## ስለውጭ አገር ሰዎች ምዝገባና መኖሪያ ፈቃድ

፳፮· ስለምዝገባ

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ መሠረት ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው ማመልከቻውን ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ ሞልቶ ከሚከተሉት ጋር አያይዞ የማቅረብ እና የሚቀርብለትን ጥያቄ በትክክል የመመለስ ግዴታ አለበት፤

ሀ) እንደአግባቡ የጸና የጉዞ ሰነድ፤

ለ) ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖርበትን ወይም ከዘጠና ቀናት በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቆይበትን ምክንያት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ፤ እና

ሐ) ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችና ሰነዶች።

፪· አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት በተጨማሪ ፎቶግራፉን መስጠት አለበት።

23. *Application for Visas*

1) Applications for diplomatic and service visas shall be submitted to the Ministry or to Ethiopian Embassies or Consular Posts abroad.
2) Applications for other visas shall be submitted to the Authority or to Ethiopian Embassies or Consular Posts abroad.
3) An application for a visa shall be made by filling in a form issued for such purpose and shall be accompanied with a valid travel document and a valid health certificate as may be necessary.

24. *Issuance of Travel Documents and Visas by Ethiopian Embassies and Consular Posts Abroad*

1) Ethiopian Embassies and Consular Posts abroad shall:
   (a) issue laissez-passer in accordance with Article 8 of this Regulation;
   (b) receive and, upon ascertaining their completeness, transmit to the Authority applications for the issuance of travel documents other than laissez-passer and diplomatic and service passports; and issue to the applicants the travel documents prepared by the Authority.
2) Ethiopian Embassies and Consular Posts abroad shall issue visas in accordance with the provisions of this Regulation and directives issued by the Ministry and the Authority pursuant to Article 38 hereof.
3) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, Ethiopian Embassies and Consular Posts shall have to obtain the consent of the Authority prior to the issuance of an immigrant visa or a student visa.

25. *Issuance of Visa at Ports of Entry*

Conditions justifying the issuance of visas at ports of entry shall be specified by directives to be issued by the Authority and the Ministry pursuant to Article 38 of this Regulation.

## PART FIVE
## *REGISTRATION OF FOREIGNERS AND RESIDANCE PERMIT*

26. *Registration*

1) An application for registration in accordance with Article 13 of the Proclamation shall be made by filling in a form issued for such purpose and the applicant shall have the obligation to attach the following and to answer truthfully to questions presented to him:
   (a) a valid travel document when relevant;
   (b) an evidence showing his reasons for residing or staying for more than ninety days in Ethiopia;
   (c) other information and documents that may be required in accordance with directives issued by the Authority.
2) The applicant shall, in addition to those required under Sub-Article (1) of this Article, furnish his photograph.

፳፯· ስለመኖሪያ ፈቃድ

፩· በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፳፮ መሠረት የተመዘገበ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው በዚህ ደንብ መሠረት የሚጠየቀውን የመኖሪያ ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ከፈጸመ በኋላ እንደሁኔታው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፰ ወይም ፳፱ መሠረት ቋሚ ወይም ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጠዋል።

፪· የመኖሪያ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም የውጭ አገር ሰው በምዝገባ ወቅት ባስመዘገባቸው መረጃዎች ላይ በተለይም የስም፣ የዜግነት ፣ የሥራ፣ የጋብቻ ወይም የሥራ ወይም የመኖሪያ አድራሻ ለውጥ ሲኖር ለውጡ ባጋጠመ በ፴ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማስታወቅ አለበት።

፫· አግባብ ባላቸው ባለሥልጣኖች በሚጠየቅበት ጊዜ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው እንደአግባቡ የመኖሪያ ፈቃዱን ፣ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬/፪/ የተመለከተውን የመታወቂያ ወረቀት ወይም ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን የጉዞ ሰነድ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፳፰· ስለቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ወይም /፪/ መሠረት በመኖሪያ ቪዛ ወደ ኢትዮጵያ ለገቡ የውጭ አገር ሰዎች ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጣል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) መደበኛ መኖሪያውን ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሠረተና ማመልከቻውን እስካቀረበበት ቀን ድረስ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ለኖረ፣

ለ) እራሱንና ቤተሰቡን ለማስተዳደር የሚያስችል ሕጋዊ የገቢ ምንጭ ላለው፣ እና

ሐ) መልካም ሥነ ምግባር ላለው፣

የውጭ አገር ሰው ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌ ቢኖርም ከኢትዮጵያ ዜጋ ጋር የፀና ጋብቻ የፈጸመ የውጭ አገር ሰው ጋብቻው ከተፈጸመ ከአንድ ዓመት ያላነሰ ጊዜ የሞላው ከሆነ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

፬· በኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ወይም በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ የተሠማራ ወይም ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ ወይም ሊያበረክት ይችላል ተብሎ የሚገመት የውጭ አገር ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪/ሀ/ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ባያሟላም ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

፭· ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ የተሰጠው የውጭ አገር ሰው አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የሥራ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጠዋል።

፳፱· ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፮ መሠረት የተመዘገበና ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጠው የማይችል ማንኛውም የውጭ አገር ሰው ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጠዋል።

፪· ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ የሚያገለግለው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ ከዚያ በላይ መቆየት ካስፈለገ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ በአዲስ መተካት አለበት።

27. *Residence Permit*

1) Any foreigner who has been registered in accordance with Article 26 of this Regulation shall, upon payment of the fee chargeable under this Regulation, be issued with either a permanent or temporary residence permit, as the case may be, in accordance with Article 28 or 29 of this Regulation.
2) Any foreigner who has been issued with a residence permit shall have the obligation to notify the Authority of the occurrence of any change in the information furnished at the time of registration, particularly a change in his name, nationality, occupation, marital status or address of work place or residence, within thirty days from the date of such occurrence.
3) Any foreigner shall have the obligation to present his residence permit or the identity card referred to in Article 14(2) of the Proclamation or his travel document with which he entered Ethiopia whenever required by the appropriate authorities.

28. *Permanent Residence Permit*

1) A permanent residence permit shall be issued to a foreigner who has entered Ethiopia by an immigrant visa as provided for in Sub-Article (1) or (2) of Article 17 of this Regulation.
2) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, permanent residence permit may be issued to any foreigner who has:
   (a) established his domicile in Ethiopia and lived in Ethiopia for at least three years preceding the submission of his application;
   (b) sufficient and lawful source of income to maintain himself and his family; and
   (c) good character.
3) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, a permanent rersidence permit may be issued to a foreigner who is married to an Ethiopian national if there is a lapse of at least one year since the conclusion of the marriage.
4) A foreigner engaged in investment or humnitarian activities in Ethiopia or who has made or is expected to make outstanding contributions in the interest of Ethiopia may be issued with a permanent residence permit irrespective of the waiting period provided for in Sub-Article 2(a) of this Article.
5) A foreigner who has obtained a permanent residence permit shall be issued with a work or an investment permit in accordance with the appropriate laws.

29. *Temporary Residence Permit*

1) A temporary residence permit shall be issued to any foreigner who has been registered in accordance with Article 26 of this Regulation and who is not entitled to a permanent residence permit.
2) A temporary residence permit shall be valid for a period not exceeding one year from the date of issuance and shall be replaced by a new one where it becomes necessary to stay longer.

፴· <u>የመኖሪያ ፈቃድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ</u>

፩· የመኖሪያ ፈቃዱ የተገኘው ሐሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ሲታወቅ ሊሠረዝ ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ከተመለከቱት በተጨማሪ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ በሚከተሉት ሌሎች ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፤

ሀ) ባለፈቃዱ ኢትዮጵያን ለቅቆ በውጭ አገር በተከታታይ ከአንድ ዓመት በላይ ከኖረ፣ ወይም

ለ) ፈቃዱ የተገኘው የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘትን ለማመቻቸት ሲባል ብቻ በተፈጸመ ጋብቻ ምክንያት ሆኖ ከተገኘ።

፴፩· <u>የመኖሪያ ፈቃድን ስለመመለስ</u>

የመኖሪያ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም የውጭ አገር ሰው ኢትዮጵያን ለዘለቄታው ለቅቆ ሲሄድ የተሰጠውን የመኖሪያ ፈቃድ ለባለሥልጣኑ መመለስ ይኖርበታል።

## ክፍል ስድስት
## ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች ስለሚጠየቁ ክፍያዎች

፴፪· <u>የክፍያዎች መጠን</u>

፩· ለጉዞ ሰነዶች የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አንድ የተመለከተው ይሆናል።

፪· ለቪዛ የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሁለት የተመለከተው ይኖራል።

፫· ለመኖሪያ ፈቃድና ልዩ ልዩ መታወቂያዎች የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሦስት የተመለከተው ይሆናል።

፬· የጉዞ ሰነድ፣ የመኖሪያ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ተበላሽቶ ወይም ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ አብቅቶ በአዲስ ሲተካ የመደበኛው ሙሉ ክፍያ ይፈጸማል፤ ሆኖም ጠፍቶ ሲተካ በመደበኛው ክፍያ ላይ ፳ ፐርሰንት ተጨምሮ ይከፈላል።

፭· በጉዞ ሰነድ፣ በመኖሪያ ፈቃድ ወይም በመታወቂያ ላይ የተፈጠረን ስህተት ለማረም የመደበኛው ሙሉ ክፍያ ይፈጸማል፤ ሆኖም ስህተቱ የተፈጠረው በባለሥልጣኑ ምክንያት ከሆነ ክፍያ አይጠየቅም።

፮· የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፹፱ የአንቀጽ ፴፪ ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚሰበሰብ ክፍያ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ ደረሰኝ ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም የተሰበሰበው ገንዘብ በተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ ፴፭ መሠረት ገቢ መደረግ አለበት።

፴፫· <u>ከክፍያ ነፃ ስለመሆን</u>

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፪ መሠረት የሚጠየቁ ክፍያዎች በሕግ ወይም በዓለም አቀፍ ውል መሠረት ከክፍያ ነጻ እንዲሆኑ የተደረጉ ሰዎችን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆኑም።

፪· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ መሠረት በይለፍ ሰነድ ወደ አገሩ ለመመለስ የሚጠይቅና የመክፈል አቅም የሌለው ኢትዮጵያዊ ከክፍያ ነፃ ይሆናል።

፫· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ መሠረት አስቸኳይ የጉዞ ሰነድ እንዲሰጠው የሚጠይቅና የመክፈል አቅም የሌለው ሰው ከክፍያ ነፃ ይሆናል።

30. *Revocation of Residence Permit*

1) A residence permit may be revoked where it is found to have been obtained by presenting false evidence.

2) A pemanent residence permit may also be revoked on the following ground:

   (a) where the holder of the permit left Ethiopia and stayed abroad for a consecutive period of more than one year; or

   (b) where the permit is found to have been obtained on the basis of a marriage of convenience.

31. *Return of Residence Permit*

Any foreigner who is holder of a residence permit shall have the obligation to return it to the Authority if he is leaving Ethiopia for good.

## PART SIX
## *FEES PAYABLE FOR VARIOUS SERVICES*

32. *Fee Rates*

1) Fees to be paid for travel documents shall be as prescribed in Schedule One of this Regulation.

2) Fees to be paid for visa services shall be as prescribed in Schedule Two of this Regulation.

3) Fees to be paid for residence permit and identification cards shall be as prescribed in Schedule Three of this Regulation

4) The full amount of the regular fee shall be paid to replace a travel document when it is damaged or has expired; provided, however, that the replacement fee shall be raised by 20% if it is lost.

5) The full amount of the regular fee shall be paid for making corrections in a travel document, residence permit or an identification card; provided, however, that no payment shall be required where the cause of the mistake could be attributable to the Auhtority.

6) Notwithstanding Article 32 of the Council of Ministers Financial Regulations No. 17/1997, payment of fees under this Article may be collected against receipt issued by the Authority; provided, however, that the proceeds thereof shall be deposited in accordance with Article 35 of said Regulations.

33. *Exemptions*

1) Fees payable under Article 32 of this Regulation shall not be applicable to persons who are exempted from payment in accordance with the law or treaties.

2) An Ethiopian returning from abroad and applying for a laissez-passer under Article 8 of the this Regulation shall be exempted from payment of fees thereof where he is unable to affor it.

3. A person applying for an emergency travel document under Article 9 of this Regulation shall be exempted from payment of fees thereof where he is unable to afford it.

## ክፍል ሰባት
## ስለመግቢያና መውጫ በሮች እና ስለኢምግሬሽን ቁጥጥር

፴፬· የመግቢያና የመውጫ በሮች

፩· ወደ ኢትዮጵያ የመግቢያ ወይም ከኢትዮጵያ የመውጫ በሮች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

ሀ) በአየር ሲሆን ፤ አዲስ አበባና ድሬዳዋ፤

ለ) በየብስ ሲሆን ፤ ሞያሌ ፤ ደወሌ ፤ ጋላፊ፤ መተማ፣ ሁመራ፣ ኦሞራቴ፣ ቶጎ ውጫሌና ዶሎ ኦዶ።

፪· አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ተጨማሪ በሮችን ሊከፍት ወይም ያሉትን ሊዘጋ ይችላል።

፴፭· በመግቢያና በመውጫ በሮች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የተመደበ የኢምግሬሽን ኦፊሰር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጡ ሰዎች በአዋጁ አንቀጽ ፫ ወይም ፮ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማሟላታቸውን ወይም እነዚህ ሁኔታዎች የማይመለከቷቸው ከሆኑ ተገቢውን የመታወቂያ ወረቀት የያዙ መሆናቸውን በመግቢያና በመውጫ በሮች ላይ ይቆጣጠራል።

፴፮· በሆቴሎችና የእንግዳ ማረፊያ አገልግሎቶች ስለሚደረግ ቁጥጥር

፩· በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው በማናቸውም ሆቴል ወይም የእንግዳ ማረፊያ አገልግሎት ለማደር ሲፈልግ የጸና የጉዞ ሰነድ በማቅረብ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ፎርም መሠረት መመዝገብ አለበት።

፪· ማንኛውም ሆቴል ወይም የእንግዳ ማረፊያ አገልግሎት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የውጭ አገር ሰው ሲያስተናግድ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ ለወከለው አካል ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፫· በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የውጭ አገር ሰውን ተቀብሎ በራሱ የእንግዳ ማረፊያ የሚያስተናግድ ተቋም የተባለውን ሰው የጉዞ ሰነድ በመያዝ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑ ለወከለው አካል ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት።

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፯· ስለሪከርድ አያያዝ

በዚህ ደንብ መሠረት ከሚሰጡ የጉዞ ሰነዶችና ቪዛዎች እንዲሁም ከውጭ አገር ሰው ምዝገባና የመኖሪያ ፈቃድ ጋር ተያይዞ በአመልካቾች የሚቀርቡ መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች አማካይነት ሊወሰዱና ሊያዙ ይችላሉ።

፴፰· መመሪያ ስለማውጣት

፩· ሚኒስቴሩና ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈጸም በየሥልጣን ክልላቸው ዝርዝር መመሪያ ለማውጣት ይችላሉ።

፪· ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ በሥራ ላይ እንዲውሉ ከመደረጋቸው በፊት ለሕዝብ ይፋ እንዲሆኑ መደረግ አለባቸው።

## PART SEVEN
## *PORTS OF ENTRY AND EXIT AND IMMIGRATION CONTROL*

34. *Ports of Entry and Exit*

1) The following shall be Ethiopian Ports of entry and exit:

(a) by air: Addis Ababa and Diredawa;

(b) by land: Moyale, Dewole, Galafi, Metemma, Humera, Omorate, Togochale and Dolo Odo.

2) The Authority may designate other ports or close the existing ones where necessary.

35. *Control at Ports of Entry and Exit*

An Immigration Officer appointed under Article 16 of the Proclamation shall, at ports of entry and exit, control persons entering into or departing from Ethiopia to ensure that they have fulfilled the requirements specified under Articles 3 or 6 of the Proclamation or, where they are exempted from such requirements, that they are holding the appropriate identification cards.

36. *Control at Hotels and Lodging Houses*

1) Any non-resident foreigner who intends to lodge at any hotel or any lodging house shall have the obligation to present his valid travel document and be registered in a form prescribed by the Authority.

2) Where a hotel or a lodging house provides accommodation to a non-resident foreigner, it shall have the obligation to report to the Authority, the organ delegated by the Authority or the nearest police station, within 24 hours.

3) Where an institution provides accommodaition to a non-resident foreigner in its own quest house, it shall have the obligation to report and present the travel document of the foreigner to the Authority, the organ delegated by the Authority or the nearest police station, within 24 hours.

## PART EIGHT
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

37. *Keeping of Records*

Information to be gathered from applicants in connection with the issuance of travel documents and visas and the registration of foreigners under the provisions of this Regulation may be taken and filed with the use of electronic devices.

38. *Power to Issue Directives*

1) The Ministry and the Authority may issue directives for the implementation of this Regulation within the bounds of their respectives jurisdiction.

2) All directives issued for the implementation of this Proclamation shall be publicized prior to their enforcement.

፴፱· ስለተሻሩ ሕጎች

የጉዞ ሰነዶችና ቪዛዎች አሰጣጥ ደንብ ቁጥር ፫፻፺፭/፲፱፻፷፫ እንደተሻሻለ/ እና የቪዛና የመኖሪያ ፈቃድ አገልግሎት ዋጋን እንዲሁም የመውጫና የመግቢያ በሮችን የሚወስነው ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፲፱፻፷፫ /እንደተሻሻለ/ በዚህ ደንብ ተሽረዋል።

፵· የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ለረጅም ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩና በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፳፮ እስከ ፳፱ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የሚጠየቁ ሁኔታዎችን ሊያሟሉ የማይችሉ የውጭ ኮሙዩኒቲ አባላት የሚመዘገቡበትና የመኖሪያ ፈቃድ የሚያገኙበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያ ወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፵፩· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

39. *Repeal*

The Issuance of Travel Documents and Visas Regulations No. 395/1971 (as amended) and the Visa and Residence Permit Fees and Ports of Entry Regulations No. 394/1971 (as amended) are hereby repealed.

40. *Transitory Provisions*

Conditions of registration and issuance of residence permit applicable to members of foreign commitees resided in Ethiopia for long periods prior to the coming into force of this Regulation and who could not meet the requirements provided for under Articles 26 to 29 of this Regulation shall be prescribed by directives to be issued by the Authority.

41. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force on the 11th day of September 2004.

Done at Addis Ababa, this 20th day of October, 2004.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## ሠንጠረዥ አንድ
## ለጉዞ ሰነዶች የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ

| ተ.ቁ. | የጉዞ ሰነዱ ዓይነት | ብር | ዶላር |
|---|---|---|---|
| ፩ | ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት | ነፃ | |
| ፪ | ሰርቪስ ፓስፖርት | ነፃ | |
| ፫ | መደበኛ ፓስፖርት<br>ሀ/በአገር ውስጥ ሲሰጥ<br>፩/ ተማሪዎች ላልሆኑ<br>፪/ ለተማሪዎች<br>ለ/ በውጭ አገር ሲሰጥ<br>፩/ ተማሪዎች ላልሆኑ<br>፪/ ለተማሪዎች | <br><br>፫፻<br>፻፶ | <br><br><br><br><br>፶<br>፳፭ |
| ፬ | የሐጂና ኡምራ መጓጓዣ ፓስፖርት | ፪፻ | |
| ፭ | የውጭ አገር ሰው ፓስፖርት | ፪፻ | |
| ፮ | የይለፍ ሰነድ | | ፳ |
| ፯ | አስቸኳይ የጉዞ ሰነድ | ፪፻ | |
| ፰ | የስደተኞች የጉዞ ሰነድ | ነፃ | |

## ሠንጠረዥ ሁለት
## ለቪዛዎች የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ

| ተ.ቁ. | የቪዛው ዓይነት | ዶላር |
|---|---|---|
| ፩ | ዲፕሎማቲክ ቪዛ | ነፃ |
| ፪ | ሰርቪስ ቪዛ | ነፃ |
| ፫ | የሥራ ቪዛ<br>ሀ/የአንድ ጊዜ መግቢያ<br>ለ/በሦስት ወር የብዙ ጊዜ መመላለሻ<br>ሐ/በስድስት ወር የብዙ ጊዜ መመላለሻ<br>መ/በአንድ ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ | <br>፳<br>፴<br>፶<br>፻ |
| ፬ | የመኖሪያ ቪዛ | ፶ |
| ፭ | የቱሪስት ቪዛ<br>ሀ/የአንድ ጊዜ መግቢያ<br>ለ/በሦስት ወር የብዙ ጊዜ መመላለሻ<br>ሐ/በስድስት ወር የብዙ ጊዜ መመላለሻ | <br>፳<br>፴<br>፵ |
| ፮ | ትራንዚት ቪዛ<br>ሀ/ለአንድ ጊዜ ትራንዚት<br>ለ/ለሁለት ጊዜ ትራንዚት | <br>፳<br>፴ |
| ፯ | የተማሪ ቪዛ | ፳ |

## ሠንጠረዥ ሦስት
## ለመኖሪያ ፈቃድና ለመታወቂያ የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ

| ተ.ቁ. | የአገልግሎት ዓይነት | ብር |
|---|---|---|
| ፩ | ጊዜያዊ መኖሪያ ፈቃድ<br>ሀ/ተማሪ ላልሆኑ<br>ለ/ተማሪ ለሆኑ | <br>፬፻<br>፪፻ |
| ፪<br>፫ | ቋሚ መኖሪያ ፈቃድ<br>የኢትዮጵያ ዜግነት በሕግ ለተሰጠው የውጭ አገር ሰው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት | ፭፻<br>፪፻ |
| ፬ | ልዩ ልዩ መታወቂያዎች | ፳ |

## SCHEDULE ONE
## FEES PAYABLE FOR TRAVEL DOCUMENTS

| No. | Type of Travel Document | Birr | USD |
|---|---|---|---|
| 1 | Diplomatic Passport | gratis | |
| 2 | Service Passport | gratis | |
| 3 | Ordinary Passport:<br>a) Issuance in Ethiopia<br>1) non-students<br>2) students<br>b) Issuance outside of Ethiopia<br>1) non-students<br>2) students | <br><br>300.00<br>150.00 | <br><br><br><br><br>50.00<br>25.00 |
| 4 | Hajj and Umrah Passport | 200.00 | |
| 5 | Alien Passport | 200.00 | |
| 6 | Laissez-Passer | | 20.00 |
| 7 | Emergency Travel Document | 200.00 | |
| 8 | Refugee Travel Document | gratis | |

## SCHEDULE TWO
## FEES PAYABLE FOR VISAS

| No. | Type of Visa | USD |
|---|---|---|
| 1 | Diplomatic Visa | Gratis |
| 2 | Service Visa | Gratis |
| 3 | Business Visa:<br>a) single entry<br>b) multiple entry for three months<br>c) multiple entry for six months<br>d) multiple entry for one year | <br>20.00<br>30.00<br>50.00<br>100.00 |
| 4 | Immigrant Visa | 50.00 |
| 5 | Tourist Visa:<br>a) Single entry<br>b) multiple entry for three months<br>c) multiple entry for six months | <br>20.00<br>30.00<br>40.00 |
| 6 | Transit Visa:<br>a) single transit<br>b) double transit | <br>20.00<br>30.00 |
| 7 | Student Visa | 20.00 |

## SCHEDULE THREE
## FEES PAYABLE FOR RESIDENCE PERMIT AND IDENTIFICATION CARDS

| No. | Type of Service | Birr |
|---|---|---|
| 1 | Temporary Residence Permit<br>a) non-students<br>b) students | <br>400.00<br>200.00 |
| 2<br>3<br>4 | Permanent Residence Permit<br>Certificate of Naturalization<br>Identification card | 500.00<br>200.00<br>20.00 |